## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 248388

ጥቅምት 13 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

**አመልካቾች፡-** 1ኛ/ አቶ ፈጠነ ዳዲ ጠበቃ ሚልዮን ግርማ ቀርቧል፡፡

2ኛ/ አቶ አረካ ፋንታሁን

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ/ አብዲ ቦሩ ኃላ.የተ.የግል ማህበር

2ኛ/ አቶ አንበሴ ዘውዴ

3ኛ/ አቶ ንጉሴ አቡ

4ኛ/ አቶ መላኩ ገ/ሚካኤል

5ኛ/ አቶ አለማየሁ ዘርጋው

6ኛ/ አቶ ይርጋ ተክሉ

7ኛ/ አቶ ደረጀ አለማየሁ

(1ኛ–7ኛ) አልተጠሩም

ለጥቅምት 21 ቀን 2016 ዓ.ም የተቀጠረው መዝገብ አመልካቾች ዕግድ እንዲሰጣቸው አቤቱታ ስላቀረቡ ቀጠሮ ተሰብሮ ተመርምሮ ተከታዩ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ትእዛዝ</u>**

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ የማኀበር አባልነት መብት ማስከበርን የሚመለከት ክርክር ሲሆን ፤ አመልካቾች የ1ኛ ተጠሪ ማኀበር አባል መሆናቸውን ገልፀው በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ ፣ ማኀበሩ ኦዲት እንዲሆንና የትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ ባቀረቡት ክስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከ1ኛ ተጠሪ ማኀበር አባልነት ተሰርዘው እያለ ከአባልነት በመሰረዛቸው የሚገባቸውን መብት ከሚጠይቁ በቀር የማኀበር አባል ነን በማለት ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት የለውም በሚል በፍ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 33(2) እና 244 መሠረት ክሳቸውን ወድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት መጽናቱን ተከትሎ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት መሰረዙን በመቃወም በሰበር እንዲታረምላቸው አመልካቾች ሰኔ 2 ቀን 2015 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ለሰበር ሰሚው ችሎት መምራቱ ለትዕዛዙ መሰጠት ምክንያት ሆኗል፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ። ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የጠየቁት ዳኝነት የመብት ምንጩ የ1ኛ ተጠሪ ማኅበር አባል በመሆን የሚገኝ ሲሆን ፤ 1ኛ አመልካች ማኅበሩ ተቋቁሞ ከሚሰራበት ቦታ ለቆ የመኖሪያ አድራሻውን ቀይሮ አዳማ ከተማ ስላገባ እና የአባልነት ግዴታውን ስላልተወጣ፤ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በራሱ ፍላጎት ባቀረበው አቤቱታ በሕጉና በመተዳዳሪያ ደንቡ መሠረት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከአባልነት መሰረዛቸው በማስረጃ መረጋገጡን ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግንዛቤ ተወስዷል። አመልካቾች የማኅበር አባልነታቸው ቀሪ ከሆነ በኋላ የ1ኛ ተጠሪ ማኅበር አባላት ብቻ መብት የሖነውን ጠቅላላ ጉባዔ እንዲጠራ መጠየቅ ፣ ማኅበሩ ኦዲት ሆኖ የትርፍ ክፍፍል እንዲደረግ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሠረት ለመክሰስ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 431044 ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር

1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10 ሥር የተመለከተውን መስፈርት ስለማያሟላ በአንቀጽ 28(2) እና ሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7(2) መሠረት ውድቅ ነው ብለናል፡፡

የሰበር አቤቱታው አያስቀርብም ስለተባለ አመልካቾች ያቀረቡት የዕግድ ይሰጠን አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዕ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !